

# ወጣቱ ባለጠጋ ሰው

አንድ ቀን አንደ ወጣት ባለጠጋ ሰው ወደኢየሱስ መጣና በእግሮቹ ስር ወድቆ ሰገደለት። “ቸር መምህር ሆይ! የዘላለም ሕይወት እንዳገኝ ምን ማድረግ ይገባኛል?” ሲል ጠየቀው። ኢየሱስም ትዕዛዛትን ሁሉ እንዲጠብቅ ነገረው። ባለጠጋው ሰውም፣ “የትኞቹን ሕግጋት?” ሲል ኢየሱስን መልሶ ጠየቀው። ኢየሱስም፣ “አትግደል፣ አታመንዝር፣ አትስረቅ፣ የሐሰት ምስክር አትሁን፣ አባትህንና እናትህን አክብር፣” ሲል መለሰለት።

ከዚያም በአስሩ ትዕዛዛት ውስጥ ያልተጨመረ አንድ ሕግ ይጠቅስለታል። ይህም ትዕዛዝ በሌዋውያን ምዕራፍ 19፡ 18 ውስጥ ያለውና፣ “ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ፣” የሚለው ነው። በዚሁ ክፍል ውስጥ ሕዝቡ ማንንም እንዳይበቀሉና ቂም እንዳይዙ ይልቁንስ ጎረቤቶቻቸውን/ባልንጀሮቻቸውን/ እንደራሳቸው አድርገው እንዲወዱ የሚጠይቅ ትዕዛዝ ነው።

ወጣት ባለጠጋውም እነኝህን ትዕዛዛት በሙሉ ከልጅነቱ ጀምሮ እንደፈፀማቸው ተናገረ። ነቀፌታ የሌለው ሕይወት ነበረው። መፅሐፍ ቅዱስ እንደሚናገረው ኢየሱስ ባለጠጋውን ሰው ተመለከተውና ወደደው። ሆኖም ኢየሱስ ወደሰውዬው ልብ ሲመለከት እውነተኛ ተከታዩ እንዳይሆን የሚከለክለው ነገር ተመለከተ።

ኢየሱስም አሁንም አንድ ነገር እንደሚቀረው ነገረው። ያለውን ሁሉ ሸጦ ለድሆች እንዲሰጥ! ይህንን ቢያደርግም በሰማይ ሀብት እንደሚኖረው ነገረው። ከዚያም ኢየሱስን መከተል ይችላል።

የባለጠጋው ሰው ፊት ሐዘን ለበሰ። እያዘነም ሄደ። ምክንያቱም እጅግ ብዙ ሀብት ነበረውና ነው። ከሀብቱ መለየት በጣም ከበደው።

ባለጠጋው ሰው ከሄደ በኋላ ኢየሱስ ክርስቶስ ለባለጠጋ ሰው መንግስተ ሰማያት መግባት በጣም ከባድ እንደሆነ ነገራቸው። እንዲህም የሚል ምሳሌ ነገራቸው፣ “ሀብታም መንግስተ ሰማያት ከሚገባ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ቢሾልክ ይቀላል።”

ይህ ታሪክ የሚገኘው በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 18፡ 18-30 ባለው ክፍል ውስጥ ነው።

http://gardenofpraise.com